# የአካባቢ ሳይንስ

## የተማሪዎች መጽሐፍ ሁለተኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ጋዲሳ በዳዳ
ቲጃኒ ሁሴን
ንጉሴ ለማ
ዘውዱ ቱሉ

### አርታኢዎች

አሰግድ ደረጀ
ጉታ ሁንዴ
ፍቃዱ ከበደ
ታርኩ ዲጋ
ግርማዬ ደፋር

### ገምጋሚዎች

አሸብር መኮንን
ብርሃኑ ለታ
ዘውዴ ረጋሣ

### ተርጓሚዎች

አበራ ከበበው
ታደሰ ዱሬሳ

### ግራፍክስ

ታደሰ ድንቁ

### እሉስቱሬተር

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ።

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል።

# ይዘት


ምዕራፍ 1: ሳይንስን ግልፅ ማድረግ ...... 1

1.1 የሰውነታችን ውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አባላተ አካል...... 1

1.2 ልዩ ቁሶችን መለየት...... 10

1.3 የብርሃን ምንጮች...... 15

ምዕራፍ 2: የወረዳችን/ የከተማ አስተዳደራችን መገኛ ...... 20

2.1 የመገኛ ምንነት ...... 20

2.2 አንፃራዊ መገኛ...... 21

2.5 በወረዳችን/በከተማ አስተዳደራችን የሚገኙ ቀበሌዎች ስምና መገኛቸው ...25

ምዕራፍ 3: ተፈጥሮአዊ አካባቢ...... 29

3.1. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ...... 29

3.3 በወረዳችን/ከተማችን የሚገኙ እንስሳት...... 49

3.5 የወረዳችን/ከተማችን የአከባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ...... 58

ምዕራፍ 4: የማህበረሰብ አካባቢ...... 65

4.1 የቤተሰብ አባላት እና ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉ ነገሮች...... 65

4.2 የትምህርት ቤት ማህብረሰብ በጋራ ሊያከናውኑ...... 73

4.3 የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና...... 77

ምዕራፍ 5: ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ...... 83

5.1 የትራፍክ ደንቦች ...... 87

5.2 የራስን ጤንነት መጠበቅ...... 87

# ምዕራፍ 1

## ሳይንስን ግልፅ ማድረግ

### 1.1 የሰውነታችን ውጫዊ አካል ክፍሎች እና የስሜት አባላተ አካል

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ |
| የሰውን ውጫዊ አካል ክፍሎች ፃፍ/ፊ |

የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች ዓይን፤ ጆሮ፤ አፍንጫ፤ ፀጉር፤ አፍ፤ እጅ፤ እግር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ተግባር 1.1

በቁጥር ተለይተው የተሰየሙትን የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች በመለየት ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡




ሥዕል 1.1 የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች

## የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች ጥቅም

| የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች | ጥቅም |
|---|---|
| ፀጉር | ለውበት፤ራስን ለመሸፈን |
| ራስ | ጭንቅላትን ለመሸፈን |
| ዓይን | ለማየት እና የተለያዩ ቀለማትን ለመለየት |
| ጆሮ | ለመስማት እና አቅጣጫን ለመለየት |
| አፍንጫ | ለማሽተት እና የተለያዩ ሽታዎችን ለመለየት |
| አንገት | ራስን ደግፎ ለመያዝ |
| እጅ | ለመብላት፣ ለመነካካትና ለመሥራት |
| ጉልበት | ለእግር እንቅስቃሴ |
| እግር | ደግፎ ለማቆም እና ለመንቀሳቀስ |

## የስሜት አባላተ አካል

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ከዚህ በታች የሚገኙትን የስሜት አባላተ አካል ስማቸውን ተናገር/ሪ



ሥዕል 1.2 አምስቱ የስሜት አባላተ አካል

የሰው አምስቱ የስሜት አባላተ አካል ዓይን፤ ጆሮ፤ አፍንጫ፤ ምላስ እና እጅ (ቆዳ) ናቸው።

## የስሜት አባላተ አካል ጥቅም

የስሜት አባላተ አካል በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ለመገንዘብ ይረዳናል።

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ከዚህ በታች ያለው ሥዕል የሚያሳየውን የስሜት አባላተ አካል ጥቅም ተናገር/ሪ።



ሀ. ዓይን



ለ. ጆሮ



ሐ. ምላስ



መ. አፍንጫ



ረ. እጅ

ሥዕል 1.3 አምስቱ የስሜት አባላተ አካል ጥቅም

## 1. ዓይን

ዓይን በአካባቢያችን ያሉትን ነገሮች ለማየት ይረዳናል



ሥዕል 1.4 የአይን ጥቅም

## 2. ጆሮ

ጆሮ የተለያዩ ድምፆችን ለመስማት ያገለግላሉ።



ሥዕል 1.5 የጆሮ ጥቅም

## ተግባር 1.2

ከዚህ በታች ያሉትን የእንስሳት ድምፅ ለጓደኛህ/ሽ አሰማ/ሚ።



ሥዕል 1.6 እንስሳት

## 1. ምላስ

ምላስ የተለያዩ ጣዕሞችን ለመለየት ያገለግላል።

ለምሳሌ፡ የሎሚ፤ የጨው፤ የስኳር፤ የብርቱካን እና የመሳሰሉትን ጣዕም በምላሳችን እንለያለን።





ሥዕል 1.7 የምላስ ተግባር

## 2. አፍንጫ

አፍንጫ የተለያዩ ሽታዎችን ለመለየት ያገለግላል።





ሥዕል 1.8 የአፍንጫ ተግባር

## 3. እጅ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የነገሮችን ሙቀት እና ቅዝቃዜ በየትኛው የስሜት አባላተ አካላት ትለያለህ/ሽ?

እጅ በመዳሰስ ነገሮችን ለመለየት የሚረዳ የስሜት አባላተ አካል ነው:: እነሱም፡ ሞቃት እና ቀዝቃዛ ነገሮች፤ ሸካራ እና ለስላሳ ነገሮችን ለመለየት ይረዳል::



ሥዕል 1.9 የእጅ ተግባር

## 1.2 ልዩ ቁሶችን መለየት

የስሜት አባላተ አካላትን በመጠቀም ልዩ ቁሶችን መለየት ይቻላል:: ይሄውም እንደ ቀለም፣ ጣዕም፣ ሽታ፣ ቅርፅ፣ መጠን፣ ጥንካሬ ያሉትን ባህሪያት መሰረት በማድረግ ልዩ ቁሶችን መለየት ይቻላል::

ተግባር 1.3

1. ከዚህ በታች ያሉትን የልዩ ቁሶች ባህሪያት በየትኛው የስሜት አባላተ አካላት መለየት እንደሚቻል ለጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ:: የልዩ ቁሶች ባህሪያት ቀለም፣ቅርፅ፣ጥንካሬ፣ጣዕም፣ሽታ ናቸው::
2. በአካባቢህ/ሽ ከሚገኙ ልዩ ቁሶች ውስጥ በቀለም፣ በቅርፅ፣ በጥንካሬ፣ በጣዕም እና በሽታ ሊለዩ የሚችሉትን ልዩ ቁሶች በመለየት ዘርዝር/ሪ::

### ሀ. ቀለም

ቀለም በዓይናችን መለየት የሚቻል የልዩ ቁሶች ባህሪይ ነው::

ለምሳሌ: ደም ቀይ ነው፣ የዕፅዋት ቅጠል አረንጓዴ ነው፣ ስኳር እና ጨው ነጭ ናቸው፣ የአደይ አበባ ቢጫ ነው






ደም የአደይ አበባ ቅጠል ጨው

ሥዕል 1.10 የተለያየ ቀለም ያላቸው ልዩ ቁሶች

## ለ. ሽታ

ሽታ አፍንጫችንን በመጠቀም ልዩ ቁሶች ለመለየት የሚያስችል ባህሪይ ነው::

ለምሳሌ:

ውሃ ሽታ የለውም

ሽቶ ጥሩ ሽታ አለው

ጥንብ መጥፎ ሽታ አለው




ጥንብ ሽቶ

ሥዕል 1.11 የተለያየ ሽታ ያላቸው ልዩ ቁሶች

## ሐ. ጣዕም

ጣዕም የልዩ ቁሶች ባህሪይ ሆኖ ልዩ ቁሶችን በምላሳችን ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡

ምሳሌ፡
ማር እና ስኳር ጣፋጭ ናቸው፡፡
ሎሚ ኮምጣጣ ነው፡፡
ጨው ጨዋማ ነው




ስኳር




ማር




ሎሚ

ሥዕል 1.12 የተለያየ ጣዕም ያላቸው ልዩ ቁሶች

**ማሳሰቢያ፡ ማንኛውም ሰው የማያውቀውን ነገር መቅመስ የለበትም፡፡**

**ተግባር 1.4**

በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ቁሶች ውስጥ:

1. የመራራነት፣
2. የጣፋጭነት እና
3. የኮምጣጣነት ባህሪይ ያላቸውን በመለየት ከዘረዘራችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ርፖርት አቅርቡ፡፡

## መ. ጥንካሬ

ጥንካሬ የቁሶች ባህሪይ ሆኖ በእጃችን በመዳሰስ ልዩ ቁሶችን ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡

**ለምሳሌ፡**

እንደ ሶፍት፣ እስፖንጅ፣ ልብስ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ላስላሳ ሲሄኑ እንደ ብረት እና ድንጋይ ያሉት ነገሮች ደግሞ ጠንካሮች ናቸው፡፡



እስፖንጅ



ድንጋይ

ሥዕል 1.13 የልዩ ቁሶች ጥንካሬ

ተግባር 1.5

ከዚህ በታች የሚገኙትን ነገሮች ጠንካራ ወይም ለስላሳ ብለህ/ሽ መድብ/ቢ።

ቡርጩቆ፣ ድንጋይ፣ ብረት፣ ሶፍት፣ ፕላስትክ፣ ጎማ

## ሠ. ቅርፅ

ቅርፅ የልዩ ቁሶች ባህሪይ ሆኖ ልዩ ቁሶችን በመነካካት ለመለየት የሚያስችል ነው።



ሥዕል 1.14 የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው ልዩ ቁሶች

## ረ. መጠን

መጠን የልዩ ቁሶችን መርዘም እና ማጠር፣ መወፈር እና መቅጠን እንዲሁም መተለቅ እና ማነስ የሚገልጽ ባህሪይ ነው:: ስለዚህ መጠንን መሰረት በማድረግ ልዩ ቁሶችን መለየት እንችላለን::



ሥዕል 1.15 የተለያየ መጠን ያላቸው ኳሶች

## 1.3 የብርሃን ምንጮች

ብርሃንን የሚያመነጩ ነገሮች የብርሃን ምንጮች ይባላሉ:: ለምሳሌ፡ ፀሀይ፣ ከዋክብት፣ አምፑል፣ ሻማ፣ ባትሪ፣ እሳት እና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው::

የብርሃን ምንጮች በሁለት የከፈላሉ:: እነሱም ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች ይባላሉ::

### ሀ. የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች

በተፈጥሮ የራሱን ብርሃን ማመንጨት የሚችሉ ነገሮች የብርሃን ምንጭ ይባላሉ

ለምሳሌ፡ ፀሐይ እና ከዋክብት



ፀሐይ



ከዋክብት

ሥዕል 1.16 የተፈጥሮ የብርሃን ምንጭ

## ለ. ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ

**በሰው የተሰራው የብርሃን ምንጭ ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ ይባላል፡፡**

**ለምሳሌ፡ ሻማ፤ ባትሪ፤ አምፑል፤ እሳት**



ባትሪ



ሻማ



አምፑል



እሳት

ሥዕል 1.17 ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ

ተግባር 1.6

በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የብርሃን ምንጮች ከዘረዘራችሁ በኋላ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ በማለት በመመደብ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

## የምዕራፍ 1 መልመጃ

**ሀ. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሺ::**

1. ፀጉር የሰው ውጫዊ አካል ክፍል ነው::
2. በአካባቢያችን የሚገኙትን ነገሮች ድምፅ በአይን በማየት መለየት እንችላለን::
3. ባትሪ ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ ነው

**ለ. በፊደል "ለ" ስር የሚገኙትን በፊደል "ሀ" ስር ከሚገኙት ጋር አዛምድ::**

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1. | ምላስ | ሀ. ለማየት |
| 2. | እጅ | ለ. ለመስማት |
| 3. | አፍንጫ | ሐ. ለመቅስ |
| 4. | ጆሮ | መ. ለማሽተት |
| 5. | ዓይን | ሠ. ለመዳሰስ |

## ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ።

1. የሰው ውጫዊ አካል ክፍል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. አንገት
   ለ. ራስ
   ሐ. ጉልበት
   መ. ሁሉም ከቁሳዊ አካል ባህርያት ውስጥ በእጃችን መለየት የምንችለው የቱ ነው ?
   ሀ. ቀለም
   ለ. ሽታ
   ሐ. ጠንካራ
   መ.ጣዕም
2. **ከሚከተሉት ውስጥ ኮምጣጣ ጣዕም ያለው ልዩ ቁስ የቱ ነው?**
   **ሀ. ማር** **ሐ.ብርቱካን**
   **ለ. ስኳር** **መ. ጨው**
3. **ከሚከተሉት ውጫዊ የአካል ክፍሎች ውስጥ ለእግር እንቅስቃሴ የሚያገለግለው የቱ ነው?**
   **ሀ. ራስ** **ሐ. አይን**
   **ለ. እጅ** **መ. ጉልበት**

4. **ከሚከተሉት የብርሃን ምንጮች ውስጥ ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ የሆነው የቱ ነው?**

**ሀ. አምፑል** **ሐ. ፀሐይ**

**ለ. ኮከብ** **መ. ጨረቃ**

## መ. ሚከተሉትን ጠያቀዎች መልስ/ሽ

1. ከዚህ በታች የሚገኙትን የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎችን ጥቅም ፃፍ/ፊ፣

ሀ. አንገት ለ. እግር

2. ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጭ የሆኑትን ፃፍ/ፊ፣

# ምዕራፍ 2

## የወረዳችን/ የከተማ አስተዳደራችን መገኛ

### 2.1 የመገኛ ምንነት

መገኛ ማለት አንድን ነገር ወይም አንድን ቦታ ከሌላ ጋር በማወዳደር የትና ወዴት እንደሚገኝ መግለፅ ማለት ነው፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

ወደቀኝ፤ወደግራ፤ወደኋላእና ወደፊት አቅጣጫዎችን በመጠቀም ጥያቄዎችን መልስ/ሺ፡፡

ቆማ ከለቺው ልጅ

1. በስተግራ በኩል ምን ይገኛል?
2. በቀኝ በኩል ምን ይገኛል?
3. በጀርባ በኩል ምን ይገኛል?
4. በፊት ለፊት በኩል ምን ይገኛል?



ሥዕል 2.1. መገኛ

## 2.2 አንፃራዊ መገኛ

በአንፃራዊ መገኛ አንድ ታዋቂ ቦታን ወይም ነገርን መነሻ በማድረግ የት እንደሚገኝ በማነፃፀር የሚገለፅበት መንገድ ነው፡፡ በአንፃራዊ መገኛ አንድን ቦታ ወደቀኝ፤ ወደግራ፤ ወደኋላ እና ወደፊት በማለት መግለፅ ይቻላል፡፡

በአንጻራዊ መገኛ በአራት ትላልቅ አቅጣጫዎች በመጠቀም መግለፅ ይቻላል፡፡ እነሱም ሰሜን፤ ደቡብ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ነቸው፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

አቅጣጫ ማለት ምን ማለት ነው?

አቅጣጫ ማለት አንድ ቦታ ወይም አንድ ነገር እንደ መነሻነት ከተወሰደው ቦታ ላይ በስተየት እንደሚገኝ የሚገለጽበት መንገድ ነው። አራት ተላላቅ አቅጣጫዎች አሉ። እነሱም ሰሜን፤ ደቡብ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ናቸው።

አራቱን አቅጣጫዎች ለመለየት

ወደ ፀሐይ መውጫ ፊታችንን በማዞር ሲንቆም፣

- ፍታችን የሚያሳየው ምስራቅ
- ኋላችን የሚያሳየው ምዕራብ
- የግራ እጃችን የሚያሳየው ሰሜን
- የቀኝ እጃችን ደግሞ የሚያሳየው ደቡብን ይሆናል።




ሥዕል 2.2. ዋና ዋና አቅጣጫዎች

**ተግባር 2.1 አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን በመጠቀም**

1. የምትኖርበት/ሪበት ቤት ከትምህርት ቤታችሁ በየት አቅጣጫ እንደሚገኝ ለክፍል ተማሪዎችህ/ሽ አሳይ/ዪ።

## 2.3 የወረዳችን/የከተማ አስተዳደራችን አንፃራዊ መገኛ

የወረዳችን አንፃራዊ መገኛ በዙሪያቸው ከሚገኙ ወረዳዎች ጋር በማነፃፀር መግለፅ ይቻላል። ለምሳሌ በ ሀ፤ ለ፤ ሐ፤ መ እና ሠ ፊደላት የተወከሉ ወረዳዎችን ቀጥሎ ከሚገኘው ካርታ ላይ ተመልከቱ።




ሥዕል 2.3 አምስት ወረዳዎችን የሚያሳይ ካርታ

**በዚህ ካርታ ላይ ወረዳ ሀ**

- ከወረዳ ሐ በስተደቡብ ይገኛል።
- ከወረዳ ሠ በስተሰሜን ይገኛል።
- ከወረዳ ለ በስተምዕራብ ይገኛል።

- ከወረዳ መ በስተምስራቅ ይገኛል፡፡

**ተግባር 2.2**

**በቡድን በመሆን፣**

1. በጎረቤታችሁ የሚገኙና ወረዳችሁን/ የከተማ አስተዳደራችሁን የሚያዋስኑ ወረዳዎች ዘርዝሩ፡፡
2. የወረዳችሁን/ የከተማ አስተዳደራችሁን መገኛ ከጎረቤት ወረዳዎች ጋር በማነፃፀር በካርታ ላይ አሣዩ፡፡

## 2.4 በወረዳችን/በከተማ አስተዳደራችን የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች መገኛ

በወረዳችን/በከተማ አስተዳደራችን ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ቦታዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ እነሱም ተራራዎች፣ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ፏፏቴዎች፣ ደኖች፣ ፓርኮች፣ ዋሻዎች፣ ሐውልቶች፣ ጥንታዊ ቤተ-መንግስት፣ የተለያዩ ታሪካዊና መዝናኛ ቦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ተግባር 2.3**

1. በወረዳህ/ሽ /በከተማ አስተዳደርህ/ሽ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ቤተሰቦችህን/ሽን በመጠየቅ ጻፍ/ፊ፡፡
2. የፃፍከውን/ሺውን ታዋቂ ቦታዎች በካርታ ላይ አሣይ/ዪ፡፡

## 2.5 በወረዳችን/በከተማ አስተዳደራችን የሚገኙ ቀበሌዎች ስምና መገኛቸው

አንድ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎችን በውስጡ ይይዛል:: የአንድ ቀበሌ መገኛ በአራቱ አቅጣጫ በዙሪያው በሚገኙ ሌሎች ቀበሌዎች ይገለፃል::

ለምሳሌ በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ቀበሌዎችን ከዚህ በታች በሚገኘው ካርታ ላይ ተመልከት::




ሥዕል 2.4 ቀበሌዎችን የሚያሳይ ካርታ

በዚህ ካርታ ላይ ቀበሌ ሀ እንደምሳሌ ወስደን ብንመለከት: በምስራቅ ቀበሌ ሐ፣ በምዕራብ ቀበሌ ሠ፣ በሰሜን በኩል ደግሞ ቀበሌ ለ ይገኛሉ::

በቀጥታ ከሀ ቀበሌ ጋር የማይዋሰኑ ቀበሌዎች ይኖራሉ:: ለምሳሌ በዚህ ካርታ ላይ ቀበሌ ሰ እና ሸ ከ ሀ ቀበሌ ጋር አይወሰኑም::

ተግባር 2.4

በወረዳህ/ሽ ወይንም በከተማ አስተዳደርህ/ሽ ውስጥ ስንት ቀበሌዎች እንደሚገኙ ቤተሰቦችህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ።

## የምዕራፍ 2 መልመጃ




በዚህ ካርታ ላይ ቁጥሮች የወረዳዎችን ስም ይወክላሉ።

ሀ. ካርታውን በመመልከት ከዚህ በታች ካሉቱ ጥያቄዎች ውስጥ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሀሰት በማለት መልስ/ሽ።

1. ወረዳ 1 ከወረዳ 4 በስተ ደቡብ ይገኛል።

2. ወረዳ 1 ከወረዳ 5 በስተሰሜን የረገኛል።

3. ወረዳ 1 ን በስተምዕራብ የሚያዋስነው ወረዳ 2 ነው።

4. ወረዳ 1 በአምስት ጎረቤት ወረዳዎች ይዋሰናል።

5. ወረዳ 1 ከወረዳ 3 በስተደቡብ ይገኛል።

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ።

1. አንድን ቦታ ከሌላ ቦታ ጋር በማነፃፀር መግለፅ ምን ይባላል?
   ሀ. የመሬት አቀማመጥ
   ለ. አንፃራዊ መገኛ
   ሐ. ርቀት
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. የአንድ ወረዳ አንፃራዊ መገኛ በምን ይገለፃል?
   ሀ. በጎረቤት ወረዳዎች
   ለ. በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች
   ሐ. በወረዳው በሚገኙ ከተሞች
   መ. በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች

3. የአንድ ወረዳ ታዋቂ ቦታ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
   ሀ. ሀይቅ
   ለ. ተራራ
   ሐ. ፓርክ
   መ. ሁሉም

4. የአንድን ወረዳ መገኛ ለመግለፅ የሚያገለግለው የቱ ነው?
   ሀ. ሰሜን፣ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ አቅጣጫዎች
   ለ. ቀኝ፣ግራ፣ ፊለፊት እና ኋላ
   ሐ. ላይ፣ታች፣ወደታችና ወደ ላይ
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## ሐ. ቀጥሎ ያሉ ጥያቄዎችን መልስ/ሽ/.

1. በወረዳህ/ሽ/ወይንም በከተማ አስተዳደርህ/ሽ ውስጥ ከሚገኙት ቀበሌዎች ውስጥ ቢያንስ አምስቱን ጥቀስ/ሺ።
2. በአራቱ አቅጣጫዎች ወረዳችህን/ሽን ከተማ አስተዳደርህን/ሽን የሚያዋስኑ ወረዳዎችን ስም ፃፍ/ፊ፡

# ምዕራፍ 3

# ተፈጥሮአዊ አካባቢ

## 3.1. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት

### ሀ. የአየር ጠባይ

**የግንዛቤ ጥያቄ:**
የአየር ጠባይ ምንድን ነው?

የአየር ጠባይ ማለት በየእለቱ፤በየቀናቱ፤በየወራቱ እና በየወቅቱ የሚታይ የአየር ሁኔታ ማለት ነው። ስለዝህ የአየር ጠባይ ተለዋዋጭ ነው። ለምሳሌ ሞቃታማ፤ ቀዝቃዛማ፤ ዝናባማ፤ ንፋሳማ፤ ዳመናማ አየር እና የመሳሰሉት ናቸው።



ዳመና



ዝናብ



ፀሃያማ



ጉም



ንፋስ



ቀዝቃዛ

ሥዕል 3.1 የአየር ጠባይ

## ለ. የአየር ንብረት

የአየር ንብረት ማለት በአንድ አከባቢ በተደጋጋሚ ለረጅም ጊዜ ሳይቀያየር የሚታዩ የአየር ሁኔታ ነው። የአየር ጣባይ እና የአየር ንብረት የማያቋረጥ ግንኙነት አላቸው። የአየር ጠባይን የሚገልጹ የአየር ሁኔታዎች የአየር ንብረት ኤለመንቶች ናቸው። እነዚህ ኤለመንቶች ሙቀት፤ ቀዝቃዛ፤ ንፋስ፤ እርጥበት፤ ዝናብ እና የመሳሰሉት ናቸው።

**ተግባር 3.1**

1. በወረዳችሁ/በከተማችሁ ውስጥ ዝናብ በብዛት የሚዘንበው በየትኞቹ ወራት ውስጥ ነው?
2. በወረዳችሁ ዝናብ የሚዘንብበት ወራት የሚያሣይ ግራፍ የሚያውቁትን ሰዎች በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች አቅርብ/ቢ።

## የአየር ንብረት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ያለው ተፅዕኖ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአየር ንብረት መለወጥ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ምን ምን ናቸው?

የአየር ንብረት መለወጥ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚከተሉትን ነገሮች ያስከትላል። እነሱም፡

- የአካባቢ አየር ሙቀት መጨመር
- ድርቅ
- የእርሻ ምርት መቀነስ እና ረሃብ
- ሰደድ እሳት
- ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ
- ጎርፍ
- የተለያዩ በሽታዎች

- የትላትሎች እና የነፍሳት ወረራ እና የመሳሰሉት ናቸው::




የነፍሳት(አንበጣ) ወረራ






ድርቅ እና የውሃ እጥረት



የውሃ ጎርፍ



የእርሻ ምርት መቀነስ





ሰደድ እሳት

ሥዕል 3.3 የአየር ንብረት መቀየር/መለወጥ ችግሮች

# የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔዎች

**የግንዛቤ ጥያቄ**
**ለአየር ንብረት መለወጥ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት ምንድን ናቸው?**

የደን መጨፍጨፍ፤ የደን መቃጠል እና ከፋብርካ የሚወጡ ጪሶች ለአየር ንብረት መለወጥ መንስኤዎች ናቸው፡፡



የደን መጨፍጨፍ



የደን መቃጠል



የፋብሪካ ጪስ

ሥዕል 3.3 የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔዎች

## በወረዳችን/ከተማችን የሚገኙ እፅዋት

በወረዳችን/ከተማችን የተለያዩ እፅዋት ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ እነደ ዋንዛ፣ ዝግባ፣ ኦዳ፣ የኮሶ እንጨት፣ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ ቲማቲም፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ሣር እና ያሉት ናቸው።

የዕፅዋት ዋና ዋና መዋቅሮች ሥር፣ ግንድ፣ አበባ፣ ፍሬ እና ቅጠል ናቸው። ይሁን እንጂ አበባ እና ፍሬ የሌላቸው እፅዋትም አሉ።




ሥዕል 3.4 የዕፅዋት አካል ክፍሎች

ተግባር 3.2

1. አንድ ትንሽ እፅዋት ከነሥሩ በመንቀል ወደ ክፍል ውስጥ አምጣ/ጪ፣
2. የዚህን እፅዋት አካል ክፍሎች በመለየት ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ንገራቸው/ሪአቸው።

**የግንዛቤ ጥያቄ**

**ለእፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?**

ለእፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን እደሆኑ ለመለየት ተግባር 3.3 እና 3.4ን ሥራ/ሪ፡፡

## ተግባር 3.3

**የሚያስፈልጉ ነገሮች : ውሃ፣ ማስመሪያ፣ አፈር፣ ሁለት ጣሳዎችና የዕፅዋት ዘር፡፡**

**የተግባሩ ሂደት**

1. ሁለት **የዕፅዋት ዘሮች በአፈር በተሞሉ የተለያዩ ጣሳዎች ውስጥ አድርግ/ጊ፣**
2. እነዚህ የበቀሉ **ዕፅዋትን** በየጊዜው ቁመታቸውን በመለካት መመዝገብ/ቢ፣
3. አንዱን የዕፅዋት ችግኝ የፀሐይ ብርሃን በሚያገኝበት ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡ ሌላኛውን የፀሐይ ብርሃን በሌለበት በጨለማ ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡
4. ሁለቱንም ችግኝ በየቀኑ እኩል የሆነ ውሃ ማጠጣት፡፡
5. እነዚህን ዕፅዋት በየቀኑ በመመልከት፣ ያየሃውን/ሺውን ልዩነት ፃፍ/ፊ፡፡

6. የዕፅዋቱን ቁመት ለማወቅ በየሳምንቱ ቁመታቸውን በማስመሪያ መለካት፡፡ ውጤቱን ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ፃፍ/ፊ፣




| ጊዜ | የፀሀይ ብርሃን ባለበት የእፅዋቱ ቁመት | በጨለማ ውስጥ የእፅዋቱ ቁመት |
|---|---|---|
| የመጀመሪያው ሳምንት | | |
| በሁለተኛው ሳምንት | | |
| በሶስተኛው ሳምንት | | |

**ጥያቄ:** በሁለቱ ዕፅዋት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?




በሁለቱ ዕፅዋት መካከል ያለው የርዝመት ልዩነት ለምን እደተፈጠረ ለመምህራችው ተናገሩ



የግንዛቤ ጥያቄ

እፅዋት ውሃ ካላገኙ ምን ይሆናሉ?

## ተግባር 3.4

**የሚያስፈልጉ ነገሮች ፡ የፕላስትክ ጠርሙስ፤ አፈር፤ ውሃ፤ አንድ አይነት ዝርያ ያለው ሁለት ችግኞች፣**

**የተግባሩ ሂደት፣**

1. በአፈር የተሞሉ የፕላስትክ ጣርሙስ ውስጥ ችግኞቹን ማብቀል፣
2. ሁለቱን ችግኞች የፀሀይ ብርሃን የሚያገኙበት ቦታ ማስቀመጥ፣
3. ከሀለቱ ችግኞች አንዱን ውሃ ማጠጣት:: ሌላኛውን አለማጠጣት:: እነዚህ ዕፅዋት ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
4. እነዚህን እፅዋት ለአንድ ሳምንት መከታተል:: ውሃ በሚጠጣ እና በማይጠጣ እፅዋት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የተገነዘብከውን/ሺውን ለክፍል ተማሪዎች በፅሁፍ አቀርብ/ቢ::


ዉሃ ያገኘ


ዉሃ ያላገኘ

እፅዋት ለማደግም ሆነ ለመኖር ውሃ፣ አየር አፈር እና የፀሐይ ብርሃን ያስፈልጋቸዋል፡፡

## የእፅዋት ምደባ በወረዳችን/በከተማችን

በአካባቢያችን ያሉትን እፅዋት በመጠናቸው እና በቁመታቸው በመለየት መመደብ ይቻላል፡፡

### ዛፎች

ዛፎች ረጃጅም፣ ጠንካራ እና ትላልቅ የሆኑ እፅዋት ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡ ፅድ፣ ኦዳ፣ ዋንዛ፣ ዝግባ፣ ግራር፣ ወይራ፣ የኮሶ እንጨት፣ ማንጎ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ግራር



ፅድ



ዝግባ

ሥዕል 3.5 ዛፎች

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ |
| በወረዳህ/ሽ ውስጥ ከሚገኙት ዛፎች የተወሰኑትን ዘርዝር/ሪ፡፡ |

## 1. ቁጥቋጦ

ቁጥቋጦ ከተለያዩ የዛፍ አይነቶች ቁመታቸው ያነሱ እፅዋት ናቸው።

ለምሳሌ፡ ጫት፣ቡና፣ፅገረዳ፣ጌሾ፣ጥጥ፣ሰንሰል እና የመሳሰሉት ናቸው።






ጫት ሰንሰል ፅጌሬዳ ቁጥቋጦ

ሥዕል 3.6 ቁጥቋጦ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በወረዳህ/ሽ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ የቁጥቋጦ እፅዋትን ዘርዝር/ሪ።

## 2. ሣራማ

ሣራማ በመጠናቸው ትናንሽ ሁነው ግንዳቸው አረንጓዴ እና ለሰላሳ የሆኑ ዕፅዋት ናቸው።

ምሳሌ፡ ሣር፣ ስንዴ፣ ሱፍ፡ ጤና አዳም እና የመሳሰሉት ናቸው።





ጤና አዳም ሣር ስንዴ

ሥዕል 3.7 ሣራማ እፅዋት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በወረዳህ/ሽ ውስጥ የሚገኙ ሣራማ እፅዋትን ዘርዝር/ሪ።

## 3. በእንጨት ላይ ሚጠመጠሙ ዕጽዋት

እነዚህ ዕጽዋት በሌሎች ዕጽዋት ላይ ተጠምጥሞ ወይም ተደግፎ የሚያድጉ ናቸው።

ለምሳሌ: በሎቄ፣ ወይን፣ ቲማቲም እና የመሳሰሉት ናቸው።





ወይን በሎቄ ቲማቲም

ሥዕል 3.8 በእንጨት ላይ ተጠምጥመው የሚያድጉ ዕጽዋት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በወረዳህ/ሽ ውስጥ በእንጨት ላይ ተጠምጥመው የሚያድጉ ዕጽዋት ስም ዘርዝር/ሪ።

## 4. በመሬት ላይ በመተኛት የሚያድጉ ዕፅዋት

የእነዚህ እፅዋት ግንዶች ራሳቸውን ችሎ መቆም ስለ ማይችሉ በመሬት ላይ ተኝቶ ያድጋሉ። እነዚህ ዕፅዋት ትላልቅ ፍሬ አላቸው።

ለምሳሌ፦ ዱባ፤ ቅል፤ ሀባብ



ዱባ



ቅል



ሀባብ

ሥዕል 3.9 በመሬት ላይ እየተኙ የሚያድጉ ዕፅዋት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአካባቢህ/ሽ በመሬት ላይ በመተኛት የሚያድጉ ዕፅዋት ስም ዘርዝር/ሪ።

ተግባር 3.5 የመስክ ጉብኝት

የትምህርት ቤትህን/ሽን ግቢ በመጎብኘት፣

1. በትምህርት ቤትህ/ሽ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ዕፅዋት ስሞችን ፃፍ/ፊ::
2. ከዚህ በላይ በተማርከው/ሺው መሰረት ዕፅዋትን በመመደብ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አቅርብ/ቢ::

## የዕፅዋት ጥቅም

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የዕፅዋት ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ዕፅዋት የተለያዩ ጥቅሞች አላቸው::

### 1. ለምግብነት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአካባቢህ/ሽ ለምግብነት የሚያገለግሉ የዕጽዋት ሥም ዘርዝር/ሪ::

እፅዋት የምግብ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ:: ለምሳሌ፡



አፕል



አቡካዶ



ሙዝ



ሎሚ



ሀባብ



ብርቱካን



ካሮት



ጥቅል ጎመን



ቀይ ሽንኩርት



ቀይ ስር



ድንች



ዱባ



በቆሎ



ስንዴ



አተር



ለውዝ



ቦሎቄ



ገብስ

ሥዕል 3.10 ለምግብነት የሚያገለግሉ ዕፅዋት

## 2. ለልብስ እና ለገመድ መስሪያ

እንደ ጋቢ፣ አንሶላ እና ቡሉኮ ያሉትን ልብሶች ከዕፅዋት መሰራት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ኬሻ እና ገመድ ከዕፅዋት ይሰራሉ፡፡



ጥጥ



ቃጫ

ሥዕል 3.11 ልብስ እና ገመድ ለመስራት የሚያገለግሉ ዕፅዋት

## 3. ለግንባታ እና ለቤት ውስጥ እቃዎች

እንደ ኮሶ እንጨት፣ ዋንዛ፣ዕድ እና ዝግባ ያሉት ዕፅዋት ለቤት እና ለቤት ውስጥ እቃዎች መስሪያ ያገለግላሉ::


ወንበር


ጠረጴዛ


መስኮት

ሥዕል 3.12 ከዕፅዋት የተሰሩ ዕቃዎች

**ተግባር 3.6**

በቤታችሁ ውስጥ ከሚገኙ ዕቃዎች ከዕፅዋት የተሰሩትን በመለየት ስማቸውን በመፃፍ ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ::

## 4. ለመድኃኒትነት

እንደ ዝንጅብል፣ እሬት፣ነጭ ሽንኩርት፣ እርድ እና ጤናዳም ያሉት ዕፅዋት ለመድኃኒትነት ያገለግላሉ::


እሬት


ዝንጅብል


ጤናዳም


ነጭ ሽንኩርት

ሥዕል 3.13 ለመድኀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፅዋት

## 5. ለእንስሳት ከለላ እና ለጥላነት

እፅዋት ለእንስሳት መኖሪያ ወይም መከለያ ሆኖ ያገለግላሉ::




ሥዕል 3.14 የእንስሳት ጥላ እና መከለያ

## 6. ለውበት

ዕፅዋት ለአካባቢ እና ለቤት መዋቢያ ያገለግላሉ::





ሥዕል 3.15 የመዋቢያ ዕፅዋት

ተግባር 3.7

በአካባቢያችሁ ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉትን ዕፅዋት አዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ::

## 3.3 በወረዳችን/ከተማችን የሚገኙ እንስሳት

እንስሳት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሆኖ መመገብ፣ መንቀሳቀስ እና መራባት የሚችሉ ናቸው፡፡ የተለያዩ ባህሪያትን መሰረት በማድረግ እንስሳትን በተለያዩ ቡድኖች መመደብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የጀርባ አጥንት ያላቸው እና የሌላቸው፣ የስርዓተ መራቦ ሂደትን እና የመኖሪያ ስፍራቸውን መሰረት በማድረግ መክፈል ይቻላል፡፡

ስለዚህ የጀርባ አጥንትን መሰረት በማድረግ የወረዳችንን/ከተማችንን እንስሳት ሁለት ዋና ዋና ቦታዎች መመደብ ይቻላል፡፡ እነሱም ደንደሴ እንስሳት እና ኢ-ደንደሴ እንስሳት ናቸው፡፡

### ደንደሴ እንስሳት

ደንደሴ እንስሳት ከጀርባቸው ውስጥ የጀርባ አጥንት ያላቸው ናቸው፡፡ እነሱም፡ አጥቢዎች፣ አእዋፋት፤ የገበሎ አስተኔዎች፤ የእንቁራሪት አስተኔዎች እና አሣዎች ናቸው፡፡

## 1. አጥቢዎች

አጥቢዎች በመዉለድ ጡታቸውን እያጠቡ የሚያሳድጉ እንስሳት ናቸው:: እነዚህ እንስሳት ፀጉር አላቸው::

ለምሳሌ: ሰው፣ በግ፣ ውሻ፣ ድመት፣ አይጥ፣ የሌሊት ወፍ እና የመሳሰሉት ናቸው::




ሥዕል 3 .16 አጥቢዎች

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ<br>በአካባቢህ/ሽ የሚገኙትን አጥቢዎች ዘርዝር/ሪ:: |

## 2. አእዋፋት

አእዋፋት ክንፍ ያላቸው እንስሳት ናቸው::

ለምሳሌ: ዶሮ፣ ጥንብ-አንሳ፣ እርግብ እና የመሳሰሉት ናቸው::







ጥንብ-አንሳ እርግብ ዶሮ

ሥዕል 3.17 አእዋፋት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአካባቢህ/ሽ የሚገኙትን አእዋፋት ተናገር/ሪ።

## 3. የገበሎ አስተኔዎች

የገበሎ አስተኔዎች ሰውነታቸው በቅርፊት መሰል ጠንካራ ቆዳ የተሸፈነ እንስሳት ናቸው።

ምሳሌ: እባብ፤ ኤሊ፤ አዞ፤ እንሽላልት እና የመሳሰሉት ናቸው።





ኤሊ እባብ



እንሽላሊት



አዞ

ሥዕል 3.18 የገበሎ አስተኔዎች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአካባቢህ/ሽ የሚገኙ የገበሎ አስተኔዎችን ተናገር/ሪ::

## 4. የእንቁራሪት አስተኔዎች

የእንቁራሪት አስተኔዎች በመሬት ላይ እና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው::

ምሳሌ: እንቁራሪት እና ጉርጥ



እንቁራሪት



ጉርጥ

ሥዕል 3.19 የእንቁራሪት አስተኔዎች

## 5. ዓሣዎች

ዓሣዎች በውሃ ውስጥ ብቻ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው።



ሥዕል 3.20 ዓሣዎች

## ኢ-ደንደሴ እንስሳት

ኢ-ደንደሴ እንስሳት ከጀርባቸው ውስጥ የጀርባ አጥንት የሌላቸው ናቸው። እነሱም እንደ ትሎች፣ ቀንዳ አውጣዎች፣ አልቂቶች፣ ሸረሪቶች እና ሶስት አፅቄዎች ያሉ ናቸው።

### 1. ትሎች

ትሎች ኢ-ደንደሴ እንስሳት ናቸው። ጥቂት ትሎች በሌሎች እንስሳት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። እነሱም እንደ የኮሶ ትል እና ወስፋት ያሉ ናቸው። የቀሩት ደግሞ ከሌሎች እንስሳት ሰውነት ውጭ ራሳቸውን ችሎ ነፃ ሆኖ ይኖራሉ። ለምሳሌ:የመሬት ትል።




ሥዕል 3.21 ትሎች

## 2. ቀንድ አውጣዎች

ቀንድ አውጣዎች ኢ-ደንደሴ እንስሳት ናቸው። እነሱም እርጥበት ባለበት ስፍራዎች ይኖራሉ።



ሥዕል 3.22 ቀንድ አውጣዎች

## 3. አልቂቶች

አልቂቶች ኢ-ደንደሴ እንስሳት ሆኖ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። አልቂቶች የከብቶችን ደም በመምጠጥ ሊኖሩ ይችላሉ።



ሥዕል 3.23 አልቂቶች

## 4. ሸረሪቶች

ሸረሪቶች ኢ-ደንደሴ እንስሳት ሆኖ ስምንት እግሮች ያላቸው እንስሳት ናቸው።



ሥዕል 3.24 ሸረሪቶች

## 5. ሶስት አፅቄዎች

ብዙዎቹ ሦስት አፅቄዎች ስድስት እግሮች አላቸው። ሰውነታቸው በሶስት ቦታ ይከፈላል።

ለምሳሌ: ንብ፤ ዝንብ፤ ቢራቢሮ



ዝንብ ንብ ፌንጣ ጉንዳን

ሥዕል 3.25 ሶስት አፅቄዎች

| የግንዛቤ ጠያቂ |
| --- |
| በአካባቢህ/ሽ የሚገኙትን ሶስት አፅቄዎችን ዘርዝር/ሪ:: |

## ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች

| የግንዛቤ ጥያቄ |
| --- |
| ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው? |

እንስሳት ለመኖር ምግብ፣ ውሃ፣ አየር እና መኖርያ ቦታ ያስፈልጋቸዋል::

## 3.4 የወረዳችን/ከተማችን የተፈጥሮ ሀብቶች

የተፈጥሮ ሀብት በተፈጥሮ የሚገኙ ነገሮች ሆኖ ሕይወትን ለመደገፍ እና የሰው ልጅ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያግዙ ናቸው:: እነሱም ውሃ፣ አየር፣ ዕፅዋት፣

እንስሳት፣ አፈር፣ማዕድናት (ብረት፣ድንጋይ፣ ነዳጅ)፣ የፀሐይ ብርሃን እና የመሳሰሉት ናቸው።




ሥዕል 3.26 የተፈጥሮ ሀብቶች

ተግባር 3.9

አምስት አባላት ባሉት ቡድን በመሆን፣

1. ወረዳችሁ ውስጥ የሚገኙትን ሀብቶች ዘርዝሩ፣
2. ከዘረዘራችሁት ሀብቶች ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶች የሆኑትንና ያልሆኑትን ከለያችሁ በኋላ ለክፍላችሁ አቅርቡ።

## 3.5 የወረዳችን/ከተማችን የአከባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ

የተፈጥሮ ሀብት እና አካባቢን ከተለያዩ ጉዳት መጠበቅ የአካባቢ ጥበቃ ይባላል።

> **የግንዛቤ ጥያቄ**
>
> የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎችን ግለፅ/ጭ?

### የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎች

**1. የደን ጥበቃ**

ደንን አለመመንጠር እና ዕፅዋትን መትከል



ሥዕል 3.27 ዕፅዋትን መትከል እና መንከባከብ

## 2. የአፈር እንክብካቤ




ሥዕል 3.28 እርከን መስራት

ተግባር 3.8

እርከን ያለው እና የሌለው መሬት መካከል ያለው ልዩነት ቤተሰቦችህን በመጠየቅ ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ::

## 3. የውሃ እንክብካቤ

የውሃን ንጽህና መጠበቅ እና ቆጥቦ መጠቀም የውሃ እንክብካቤ ይባላል::

## 4. ወደ አዳዲስ ምርቶች በመቀያየር እና መልሶ መጠቀም

በአካባቢያችን ተጥሎ አካባቢን ሊበክሉ የሚችሉትን ቁሶች ወደ ፋብሪካ በመመለስ ወደ አዲስ ምርት በመቀየር መጠቀም ይቻላል::

ለምሳሌ፡- ወረቀት፣ ብረት፣ ጎማ፣ መስታወት፣ ብርጭቆዎች ፣ የፕላስቲክ እና መስታወት ጠርሙሶች፣ ወዘተ ናቸው።




ሥዕል 3.29 የተጣሉ ነገሮችን ወደ አዲስ ምርት መቀየር

በሌላ በኩል ለሌላ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉትን ያገለገሉ ቁሶች ደግሞ መልሶ ስራ ላይ ማዋል ይቻላል።
ለምሳሌ፡- የፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ የመስታወት ጠርሙሶች፣ ጀርካኖች፣ወዘተ ናቸው።



ሥዕል 3.30 የተጣሉ ነገሮችን መልሰው ጥቅም ላይ ማዋል

## 5. ቆሻሻዎችን ወደ መዳበርያነት በመቀየር መጠቀም




ሥዕል 3.31 ቆሻሻን በማበስበስ ወደ መዳበርያ መቀየር

| |
|---|
| ተግባር 3.9 |
| በአካባቢህ ተጥለው አካባቢን ማቆሸሽ የሚችሉ ነገሮችን ተናገር/ሪ:: |

## የምዕራፍ 3 መልመጃ

**ሀ. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሐሰት” በማለት መልስ።**

1. ሰደድ እሳት እና ድርቅ የሚፈጠረው በአየር ንብረት ምክንያት ነው።
2. ዕፅዋት ያለ ፀሐይ ብርሃን ማደግ አይችሉም።
3. ሣራማ ዕፅዋት ትላልቅ ግንድ ያላቸው ዕፅዋት ናቸው
4. የተሰባበሩ የፕላስትክ እና መስታወት ጠርሙሶች ወደ አዳዲስ ምርቶች ሊቀየሩ አይችሉም።
5. እፅዋት መትከል እና እርከን መስራት የአፈር ጥበቃ ዘዴ ነው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ።**

1. በየጊዜው የሚቀየረው አየር ምን ይባላል?

ሀ. የአየር ንብረት
ሐ. ወቅቶች
ለ. የአየር ጸባይ
መ. ሁሉም

2. የአየር ጠባይ ምሳሌ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በጋ
ለ. ደመናማ
ሐ. ክረምት
መ. በልግ

3. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የጎርፍ አደጋ
ሐ. ድርቅ
ለ.የዝናብ እጥረት
መ. ሁሉም

4. ከሚከተሉት እንስሳት ውስጥ ኢ-ደንደሴ የሆነ የቱ?

ሀ.እባብ
ሐ. እንቁራሪት
ለ. ፍየል
መ. ንብ

5. ከሚከተሉት ውስጥ ለእንስሳት ኑሮ አስፈላጊ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አየር
ሐ. መጠለያ
ለ. ውሃ
መ. ሁሉም

6. ከዚህ በታች ከሚገኙት እፅዋት ውስጥ ልብስ ለመስራት የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ጥጥ
ሐ. ዝንጅብል
ለ. ገብስ
መ. ዝግባ

7. ከሚከተሉት ዕቃዎች ውስጥ መልሰው ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ጠርሙስ
ሐ. ብረት
ለ. ወረቀት
መ. ምግብ

## ሐ. በሬደል "ለ" ስር የሚገኙትን በሬደል "ሀ" ከሚገኙት ጋር አዛምድ

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. አጥቢዎች | ሀ. ፍየል፤ ድመት |
| 2. የገበሎ አስተኔዎች | ለ. ጉርጥ፤ እንቁራሪት |
| 3. የእንቁራሪት አስተኔዎች | ሐ. ሰጎን፤ ዶሮ |
| 4. አእዋፋት | መ. አዞ፤ እባብ |
| 5. ሶስት አፅቄዎች | ሠ. ቢራቢሮ፤ ዝንብ |

## መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

1. የአየር ንብረት እና የአየር ፀባይ ልዩነት ግለጽ/ጪ።
2. ለዕፅዋት እድገት እና መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?
4. በአካባቢህ/ሽ የተለያዩ ቆሻሻዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉባቸውን ዘዴዎች ዘርዝር/ሪ።

# ምዕራፍ 4

# የማህበረሰብ አካባቢ

## 4.1 የቤተሰብ አባላት እና ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉ ነገሮች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የቤተሰብ አባላት እነማን ናቸው?

የቤተሰብ አባላት የሚባሉት አባት፤ እናት፤ ልጆች እና ሌሎች ከእነሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እያንዳንዳቸው በቤተሰብ ውስጥ የየራሳቸው የሆነ የስራ ድርሻ አላቸው።



ሥዕል 4.1 የቤተሰብ አባላት

## ሀ. ለቤተሰብ ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች እና ጥቅማቸው

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ለቤተሰብ ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ለቤተሰብ ኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ምግብ፤ ልብስ፤ መጠለያ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለቤተሰብ ጤና አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮች ንፅህና፤ የአካል እንቅስቃሴ፤ በቂ የሆነ እረፍት፤ በቂ የሆነ እንቅልፍ፤ የተመጣጠነ ምግብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የቤተሰብ ጤንነትን መጠበቅ ያለው ጥቅም

### የብተሰብ ንፅህና

የተስተካከለ ኑሮ ለመኖር የቤተሰብ ንፅህና መጠበቅ አስፈላጊ ነው.



የገላ እና የልብስ ንፅህና



ንፁህ የሆነ መኖሪያ ቤት



የመኖሪያ ቤት አከባቢ ንፅህና



የመኖሪያ ቤት ውስጥ ዕቃዎች ንፅህና



ንፁህ የሆነ ምግብ እና ውሃ



ንፁህ የሆነ ሽንት ቤት

ሥዕል 4.2 የቤተሰብ ንፅህና

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በንፅህና ጉድለት ምክንያት በቤተሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

በንፀህና ጉድለት ምክንያት የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንደ ተቅማጥ፣ ታይፎይድ፣ የአይን በሽታ እና የመሳሰሉት ቤተሰብን ሊጎዱ ይችላሉ።



ሥዕል 4.3 በንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ ችግሮች

## የአካል እንቅስቃሴ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአካል እንቅስቃሴ ምንድነው?

የአካል እንቅስቃሴ ለጤና እና ለቤተሰብ ኑሮ በጣም አስፈላጊ ነው።

የአካል እንቅስቃሴ ለቤተሰብ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል።

- ጤናማ የሆነ ቤተሰብ ይፈጥራል።
- በቤተሰብ ውስጥ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።
- ጥሩ እንቅልፍ እና የመሳሰሉት ናቸው።



የገመድ ዝላይ





ክብደት ማንሳት



ፑሻፕ



የውሃ ዋና



ሩጫ



የኳስ ጫወታ

ሥዕል 4.4. የአካል እንቅስቃሴ

## በቂ የሆነ እረፍት እና እንቅልፍ ማግኘት

ለቤተሰብ በቂ የሆነ እረፍት እና አንቅልፍ ያስፈልጋል





ሥዕል 4.5 እረፍት እና እንቅልፍ

## ለ. የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት

የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት የሚባሉት ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ቤት ሐላፊዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞች ናቸው::




ሥዕል 4.6 የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት

**ተግባር 4.1**

የትምህርት ቤትህን/ሽን ማህበረሰብ አባላት በመዘርዘር ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ::

## ሐ. የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ

በትምህርት ቤት አቅራቢያ የሚኖሩ ሰዎች የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ ተብለው ይጠራሉ:: እነሱም አርሶ አደሮች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ ነጋዴዎች እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ::

**ተግባር 4.1**

በቡድን በመሆን በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ የሚገኙትን የማህበረሰብ አባላት በመዘርዘር ለክፍላችሁ አቅርቡ::

## 4.2 የትምህርት ቤት ማህብረሰብ በጋራ ሊያከናውኑ የሚችሉት ተግባራት

### ሀ. ጓደኝነትን ለማጎልበት የሚረዱ ተግባራት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ጓደኝነትን ማዳበር ለምን ይጠቅማል?

ጓደኝነት እርስ በርስ ለመተሳሰብ እና ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ያገለግላል::

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ጓደኝነትን እንዴት ሊናዳብር እንችላለን?





በጋራ መጫወት



በጋራ  መማር



በጋራ መስራት





በጋራ ማጥናት    በክበባት ውስጥ በጋራ መሳተፍ

ሥዕል 4. 7 ጓደኝነትን የሚያዳብሩ ተግባራት

## የትምህርት ቤት ደንቦችንና ሥርዓትን ማክበር

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የትምህርት ቤት ደንብና ሥርዓት ማክበር ለምን አስፈለገ?

### 1. የክፍል ውስጥ ደንብ

- አብረው የሚማሩ ተማሪዎችን ማክበር፣
- መምህራኖችን ማዳመጥ፣
- ጥያቄ ለመጠየቅና ለመመለስ እጅ ማውጣት፣
- የክፍል እና የቤት ሥራ መስራት፣
- ክፍል ውስጥ በጊዜ መገኘት፣
- የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት አለመንካት፣
- ፈተና አለመኮረጅ

## 1. ከክፍል ውጪ ተማሪዎች ሊያሳዩት የሚችሉ ባህሪያት

- የትምህርት ክፍለ ጊዜ ማክበር፣
- የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ፣
- የሰንደቅ ዓላማ ሥርዓት ማክበር፣
- የትምህርት ቤት ንብረቶችን መንከባከብ እና በጥንቃቄ መጠቀም፣
- የተማሪዎችን መፅሐፍ በጥንቃቄ መጠቀም፣
- ሽንት ቤትን በአግባቡ መጠቀም፣
- የትምህርት ቤቱን ንፅህና መጠበቅ፣
- የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማክበር፣
- የጫወታ ደንቦችን ማክበር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የትምህርት ቤት ደንቦችንና ሥርዓትን ማክበር ቀጥሎ ያለውን ጥቅም ይሰጣል፡፡

- የተማሪዎችና የትምህርት ቤትን ሰላም ለማስከበር፣
- የመማር ማስተማር ሂደትን በአግባቡ ለማስኬድ፣
- ሐላፊነት መቀበል የሚችሉ ተማሪዎችን ለማፍራት
- በአጠቃላይ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ይረዳል፡፡

## 4.3 የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና

የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህናን መጠበቅ የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡

- ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል፣
- በሽታን የሚያስተላልፉ ነፍሳት መራቢያቸውን ማጥፋት፣
- አካባቢ ውበት እንዲኖረው ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

> **የግንዛቤ ጥያቄ**
> የግል እና የትምህርት ቤት ንፅህና እንዴት መጠበቅ ይቻላል ?

### የግል ንፅህናን መጠበቅ

የግል ንፅህና መጠበቅ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባር ያጠቃልላል፡፡

- ገላን በየጊዜው መታጠብ፣
- የልብስ ንድፅህናን መጠበቅ፣
- ከምግብ በፊት እና በኋላ አጅን መታጠብ፣
- የጥርስ ንፅህናን መጠበቅ፣
- ጥፍርን በየጊዜው መቁረጥ፣

- ከሽንት ቤት መልስ እጅን በውሃና በሣሙና መታጠብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የትምህርት ቤት አካባቢ ንፅህና መጠበቅ

የትምህርት ቤት እና አካባቢ ንፅህና ቀጥሎ በተዘረዘሩት መንገዶች መጠበቅ ይቻላል፡፡

- የትምህርት ቤት ግቢ እና መማሪያ ክፍሎችን ማፅዳት፣
- ሽንት ቤቶችን በማፅዳት መጠቀም፣
- የተለያዩ ቆሻሻዎችን በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አለመጣል፣
- ቆሻሻዎች የሚጣሉበትን ቦታ በማዘጋጀት መጠቀም እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ሥዕል 4.8 የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ማጽዳት

## የምዕራፍ 4 መልመጃ

**ሀ. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሺ::**

1. አርፍዶ ትምህርት ቤት መሄድ የትምህርት ቤቱን ሕግ እና ደንብ አለማክበር ነው::
2. ቤተሰብ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል ነው::
3. በጋራ መስራት ጓደኝነትን ያጠናክራል::

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ::**

1. የቤተሰብ የአካል እንቅስቃሴ ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. የሰውነት ክብደት መጨመር

    ለ. እንቅልፍ ማሳጣት

    ሐ. የቤተሰብ ግንኙነትን ማጠናከር

    መ. የምግብ ፍላጎትን መቀነስ

2. የቤተሰብን ጤና ለመጠበቅ የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ንፅህና　　　　ሐ. በሽንት ቤት መጠቀም

ለ. የአካል እንቅስቃሴ　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. መምህራን　　　　ሐ. አርሶ አደር

ለ. ተማሪዎች　　　　መ. የጥበቃ ሰራተኛ

4. በትምህርት ቤት ውስጥ ጓደኝነትን ለማጠናከር የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. አለመጫወት　　　　ሐ. በጋራ መማር

ለ. ለብቻ ማጥናት　　　　መ. በግል መስራት

5. የመማሪያ ክፍል ደንብ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በሰንደቅ አላማ ስነ-ስርዓት መገኘት

ለ. እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅ

ሐ. የጫዋታ ስርዓትን ማክበር

መ. ሽንት ቤትን በአግባቡ መጠቀም

6. የግል ንፅህና መጠበቅ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.እግር መታጠብ　　　　ሐ. ገላን መታጠብ

ለ. እጅ መታጠብ　　　　መ. ሁሉም

## ሐ. ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ፤

1. ለቤተሰብ ጤና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ዘርዝር/ሪ።
2. የግል ንፅህና ምን ምንን ያጠቃልላል?
3. የግልና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ያለው ጠቀሜታ ዘርዝር/ሪ።

# ምዕራፍ 5

## ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

### 5.1 የመንገድ አጠቃቀም ጥንቃቄ

#### የትራፍክ ደንቦች

በመኪና መንገድ ላይ የትራፍክ ደንቦችን ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው። የትራፍክ ደንቦች የሚባሉት፤

1. በመኪና መንገድ ላይ ግራውን ይዞ መጓዝ



ሥዕል 5.1 ግራ መንገድ ይዞ መጓዝ

2. የመኪና መንገድን ስናቋርጥ በዜብራ ላይ ብቻ መሆን አለበት፤

የዜብራ ምልክት በአስፋልት መንገድ ላይ በነጭ እና ጥቁር ቀለም እንድታይ ተድርገው ተሰምረው ይገኛል፡፡



ሥዕል 5.2 በአስፋልት ላይ የሚገኝ የዘብራ ምልክት

3. በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት

በመኪና መንገድ ላይ መጫወት ለመኪና አደጋ ያጋልጣል፡፡



ሥዕል 5.3 የመኪና አደጋ

4. የመኪና መንገድን ሲናቋርጥ ግራእና ቀኝን በመመልከት በጥንቃቄ መሻገር፤



ሥዕል 5.4 በጥንቃቄ የመኪና መንገድ ማቋረጥ

5. የትራፍክ መብራት ምልክቶችን መከታተል፤

ሀ)




ለ)




ሥዕል 5.5 የትራፊክ መብራት ምልክት፡ ሀ) ለመኪና፣ ለ) ለሰው

6. የመኪና መንገድን ስታቋርጥ በመንገዶች ዳር የቆሙ መኪናዎች ፊት እና ኋላ ሌሎች መኪናዎች አለመኖራቸውን በማረጋገጥ በጥንቃቄ መሻገር፤
7. በመኪና መንገድ ዳር ለእግረኛ በተዘጋጀው መንገድ ላይ ብቻ መጓዝ፤



ሥዕል 5.6 የእግረኛን መንገድ ይዞ መጓዝ

## የትራፍክ ህግን ባለማክበር የሚመጡ አደጋዎች

የትራፍክ ህግ አለማክበር በሰው ህይወት እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።



ሥዕል 5.7 የትራፊክ አደጋ

**ማሳሰቢያ፡** የትራፊክ ህጎችን አለማክበር የአካል ጉዳት፣ ሞት እና የንብረት ውድመትን ሊያስከትል ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### ተግባር 5.1

በቡድን በመሆን፣

1. ለትራፊክ አደጋ የሚያጋልጡ ድርጊቶችን ዘርዝሩ፣
2. የትራፊክ አደጋ መከላከያ ዘዴዎችን በመዘርዘር ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

## 5.2 የራስን ጤንነት መጠበቅ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ጤንነት ምንድነው? በሽታስ?

ጤንነት ማለት በአካል፣ በአዕምሮ እና በማህበራዊ ኑሮ ሰላም መሆን ነው፡፡ አንድ የሰውነታችን አካል ጤናማ ነው የሚባለው የሚጠበቅበትን ተግባር ማከናወን ሲችል ነው፡፡ በሽታ ማለት ደግሞ የጤንነት መታወክ ነው፡፡

**የበሽታ መከላከያ ዜዴዎች**

### 1. የግል እና የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ

የግል እና የአካባቢ ንፅህናን ባለመጠበቅ የሚመጡ በሽታዎች ስላሉ ንፅህናችንን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

## 2. ስለት ያላቸው ዕቃዎችን በጋራ አለመጠቀም፤

እንደ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ያሉት በሽታዎች በደም ንክኪ ሊተላለፉ ስለሚችሉ ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም ለበሽታ ያጋልጣል።

ለምሳሌ፡ መርፌ፤ ምላጭ፣ ወስፌ እና የመሳሰሉትን ስለት ያላቸውን ዕቃዎች በጋራ መጠቀም እንደ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላሉት በሽታዎች ሊያጋልጡን ይችላል።

ስለዚህ ስለት ያላቸውን እቃዎች በጋራ ባለመጠቀም እና ከደም ንክኪ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል።



ምላጭ



መርፌ



ስርንጅ



መቀስ

ሥዕል 5.8 ስለታማ ዕቃዎች

ተግባር 5.2

በደም ንክኪ ሊመጡ የሚችሉትን በሽታዎች እንዴት መከላከል እንደሚቻል ቤተሰቦችህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ፡፡

## የምዕራፍ 5 መልመጃ

**ሀ. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልስ/ሺ።**

1. በመኪና መንገድ ላይ ግራውን ይዞ መጓዝ ለመኪና አደጋ ያጋልጣል።
2. የደም ንክኪ ለተላላፊ በሽታዎች ሊያጋልጥ ይችላል።
3. ኤች አይ ቪ/ኤድስ በደም ንክኪ አይተላለፍም።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ።**

1. ከሚከተሉት ድርጊቶች ውስጥ በደም ንክኪ ለሚተላለፉ በሽታዎች የሚያጋልጠው የቱ ነው?

   ሀ. በጋራ መማር

   ለ. ስለትማ ዕቃዎችን በጋራ መጠቀም

   ሐ. በጋራ መመገብ

   መ. በጋራ መጫወት

2. የሰው ትራፊክ መብራት ምልክትን በተመለከተ ሰው መንገድ እንዲያቋርጥ የሚፈቅደው ምን አይነት መብራት ሲበራ ነው?

ሀ. ቢጫ                    ሐ. ቀይ

ለ. አረንጓዴ                 መ. ሁሉም

3. የትራፍክ ደንብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በመንገድ ላይ መጫወት

ለ. በእግረኛ መንገድ ላይ መጓዝ

ሐ. የመኪና መንገድን በዘብራ ብቻ ማቋረጥ

መ. ቀኝ እና ግራን በመመልከት መንገድን ማቋረጥ

## ሐ. ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ።

1. የመኪና መንገድ ትራፍክ ደንቦችን ጻፍ/ፊ።
2. ለትራፊክ አደጋ ሊያገልጡ የሚችሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?